# ለምንስ ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?

በስልክ በድረገፅ፤ በአፍ በፅሁፍ ውሸት በዝቷል:: በወያኔ ሀቅ ለምኔ ነውና ሁሉንም ቅጥፈት በተመለከተ በየጊዜው በፅሁፍም በራዲዮም ምላሽ ለመስጠት መጣራችን የሚታወቅ ነው:: በኢሕአፓ ላይ የሚነዛው የማያቋርጥ ውሸት በወያኔም፤ በቀይ ሽብርተኛው አገዛዝና ርዝራዦቹ፤ ኢሕአፓን ካላስጠሉ ፖለቲካ ጡንቻ አናገኝም ብለው በሚያምኑ ቡድኖችና በባዕድ  ቅጥረኞች ሁሉ ነው:: በመደጋገሙ ብዛት እውነት የሚመስላቸው ወጣቶች መኖራቸው ደግሞ የሚያከራክር አይደለም:: ውሸቱ ያስፈለጋቸው ለሁሉም በምክንያት ነው:: ግማሹ ወንጀሉን ለመሸፋፈን፤ ቆሻሻ ታሪኩን ለመደበቅ፤ ሌላው ደግሞ ኢሕአፓን ለማስጠላትና ከሕዝብ ለመነጠል ነው::

በኢሕአፓ ላይ ሀሰት ወሬን በማናፈስ የመጀመሪያውን ቦታ የያዘው ደርግ ነበር:: አለምክንያትም አልነበረም:: ኢሕአፓ ሕዝብን አደራጅቶ ለትግል ስላስነሳና ደርግ ቦታውን ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት እንዲለቅ ያቀረበው ጥሪ ሰፊ ድጋፍን ለማግኘት በመቻሉ ነበር:: በመሆኑም ድርጅቱን ለማሰጠላት አንዴም አስገንጣይ ሲለው፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሶማሊያን ወረራ ደገፈ ብሎ ሲቀጥፍ፤ የሲአይኤና የአረብ ቅጥረኛ ብሎ ሲወነጅለውና አልፎም ፀረ ኦሮሞ ፀረ ጭቁን፤ የአማራ ትምክህተኛ ቡድን ብሎ  በመኢሶንም ድጋፍ ሲከሰው ነበር:: ትምክህተኛ የአማራ ቡድን የሚለውን ወያኔም ተቀብሎ ኢሕአፓን አባ ኢትዮጵያ ቡድን ብሎ ሰይሞና፤ በኢሕአፓ ውስጥ የነበሩትን ብዙ ሺ የትግራይ ተወላጆች የሸዋ ኮራኩር ብሎ ሰይሞ ሊያጥላላ ተነሳ:: በቅርቡ አንድ የቀድሞ የወያኔ መሪ ከኢሕአፓ ጋር በአዲስ አበባ ተገናኝተን የተለያየነው ኢሕአፓ በከተማ እታኮሳለሁ ሲል እኛ ደግሞ የለም ከገጠር ወደ ከተማ በማለታችን ብሎ የለፈፈው ጭልጥ ያለ ውሸት ሲሆን (የኢሕአፓ አመራር ከወያኔ ጋር በከተማ መቸም አልተገናኘምና) በሁለቱ ድርጅቶች መሀል የተፈጠረው ዋነኛው ልዩነት ወያኔ ሁሉም ብሄረሰብ ተገንጥሎ የራሱን መንግስት ያቋቁም በማለቱና ብሄረሰቦች አብረው ሊኖሩ አይችሉም የሚል መርህ ግብሩ በማውጣቱ ነበር:: ኢሕአፓ ብሄረሰቦችን አቀፍ የሆነ ከትምክህትና ከጠባብነት የራቀ ድርጅት ነበር:: በውስጡ የተሰለፉት ከልዩ ልዩ ብሄረሰቦች የመጡ እነደነበሩ ዓለም ያውቀዋል:: ኢሕአፓ ጠባብ ብሄረተኛነትን ተዋጋ እንጂ አላቀፈውም--ለዚህም ነው የጠባቦች ርብርቦሽ በኢሕአፓ ላይ የጠነከረወና እስከዛሬም ያላባራው:: የሶማሊያን

ተስፋዬ አቅዋም ደግፎ ናዝሬት/አዳማ ሳይቀር የሶማሌ ግዛት ነው ብሎ ሞቃዲሾ የተፈራረመው ወያኔ አንጂ ኢሕአፓ አልነበረም፡፡ ኢሕአፓ የዚያድ ባሬን ወረራ ተቃወመ አንጂ አልደገፈም፤ የኢሕአፓ አባላት ወረራውን ሲዋጉ ረገፉ እንጂ ለባዕ ድ ጦርድጋፍ አልሰጡም፡፡ የኢሕአፓ አባላት በሶማሊያ ስደተኛ ሰፈሮች ተሰቃዩ እንጂ ወዳጅ ተብለው እንደ ወያኔ አባላት በእንክብካቤ አልተያዙም፡፡ አረመኔው መንግስት በኦጋዴን ጦርነት አስታኮ ኢሕአፓን ሊያጠቃ ሲነሳ ኢሕአፓ ባዕድ ወራሪን ደገፈ ብሎ ለራሱ አመቺ የሆነውን የሀሰት ዜና ሲነዛ ዛሬም ይህን ሀቅ ብለው የሚያስተጋቡ መኖራቸው አጠያያቂ ነው፡፡ በሀገራችን ላይ የባዕድ ኢምፔሪ ያሊስት ቁጥጥር ይወገድ በሎ የታገለው ኢሕአፓም በአሜሪካ የስለላ ድርጅት ሊደገፍ የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ይህን በሬ ወለደ ግን በማስተጋባት አንድ የቀይ ሽብ ር ወንጀለኛ የሆነ ግለሰብ በቅርቡ በፃፈው ምስክርነት ተብዬ አሳፋሪ መፅሀፍ ውስጥ የኢሕአፓ መስራቾች ራሳቸው የምዕራብ ጀርመንና የአልጄሪያ ተቀጣሪዎች ነበሩ ሲል ዋሽቷል፡፡ ውሸት አንዳንዴ ትንኝን አወፍሮ ዝሆን ያደርጋል ነውና በአብዛኛ ው ኢሕአፓ ላይ የሚነዛው ውሸት የፈጠራ ለመሆኑ ይህ ዓይነታ ምስክር ነው፡፡ ለምንስ ይዋሻል? የራስን ወንጀል ለመደበቅ፡፡ ሀሰትን አሰራጭቶ ድርጅትን ለማስ ጠላትና አዲሱን ትውልድ ከድርጅቱ ለመነጠል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ዛሬ ድረስ ወያኔዎችና የደርግ ርዝራዦች እንደ መስኮብ ቀኖና የሚያነበንቡት ደግሞ ኢሕአፓ ወጣቱን አስጨረሰ የሚለውን ይመለከታል፡፡ ይህ አስጨረሰ የሚል ክስ የሚቀርበው ሕዝብን በጨረሱና በፈጁ ወይም በሽብሩ ተባባሪ በሆኑት ሁሉ መሆኑ የሚደበቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ኢሕአፓ ለመከላከል አንዲትም ጥይት ከመተ ኮሱ በፊት ደርግ አባሎቹን እነ ሻለቃ አሊ  ሙሳ፤ ጌታቸው ሺበሺና ሌሎች ነፍሰ ገዳይ ቡድኖችን አሰማርቶ አያሌ የኢሕአፓ አባላትን በየቦታው መጨረሱን አያነሱ ም፡፡ ዛሬ በየድርጅቱ ተሰግስገው ያሉት ነፍሰ ገዳዮችና ወንጀለኞች፤ በወያኔ ዙሪያ ያሉትም እነ ተከስተ ና ተስፋዬ ቼንቶዎች፤  በስደት ዓለም ያሉ ሽብርተኞች ሁሉ ደርግ በኢሕአፓ ላይ በቅደሚያ ጦርነት ማወጁንም አያነሱም፡፡ ይባሰ ብለው ሽብር መካሄዱን ራሱንም እስከመካድ ደርሰዋል፡፡ ደርግን ብረት በእጅህ ነውና ፍጅ ብለው ያማከሩ ምሁሮችም ዛሬ ዞር ብለው ኢሕአፓ በነጭ ሽብር ይከሰስ ብለው በቀይሽብር ተካፋይ የነበረውን ወያኔ ወትዋች ሆነዋል፡፡ ያንን የታገለ ትውልድ

ሲያብጠለጥሉም ያ ጀግና ትውልድ ደረቱን ለጥይት ሲሰጥ እነሱ የበረሀ ዓይጥ ኑሮ ን አሊያም ከደርጉ ትብብርን መርጠው እንደነበር እንዲነሳ አይፈልጉም። ስደት ለቅጥፈት ያመቻቸው ብዙዎች ህይወቱን ለአላማውና ለሕዝብ የሰጠውን ትውልድ ሲያክቸለችሉ ሀፍረትም የሚሰማቸው አልሆኑም። ኢሕአፓ ወያኔን ሲፋለም ለወያኔ ገንዘብ ሲለግሱ እንደነበርም አያምኑም።

ዴሞክራሲ ደብዛው በጠፋበት ሀገር አምባገነንነትን መዋጋት የግድ መስዋዕትነትን ይጠይቃልና የኢሕአፓ አባላት አረመኔውን ደርግ ሲታገሉ ተሰውተዋል፣ በእስር ስየል ተቀብለዋል፣ ተንገላተዋል፣ተሰደዋል። ትግል ከንቱ ወሬ ሆኖ ከተገኘ ፣ በፅናት ጠላትን መታገል ሳይሆን ከጠላት ጋር ነጋ ጠባ መደራደር፣ ሰነድ መፈራረ ምና መሽመጋገል ከሆነ በርግጥም መሰዋዕትነትን ላይጠይቅ ይችላል። ይህም ቢሆን ግን በ1997 እንዳየነው ህይወት መጠየቁ አልቀረም። ከ 200 መቶ በላይ ዜጋ በአዲ ስ አበባ ብቻ ተፈጅቷል-- ለዚህ ተጠያቂ ግን ቅንጅትም ህብረተም ሳይሆኑ አረመ ኔው ወያኔ ነው ። በደርግ ጊዜ ለተፈጀው ሕዝብ ተጠያቂው አራጁ ደርግ እንጂ ያታገለውና ደርግን የታገለው ኢሕአፓ ሊሆን አይችልም። ነገ በወያኔ ላይ የተፋፋ መ ትግል ቢከሰት ወያኔ ለሚያጠፋው ህይወት ተጠያቂው የሚየታግለው ወይም የሚያታግሉት ድርጅቶች ናቸው ከተባለማ ከወዲሁ ለወያኔ እንጎንበስን መምከሩ ያዋጣል። ሞት ለፋሺስት ብሎ ደረትን ለጥይት መሰጠት፣ አላጋልጠም ብሎ መርዝ ውጦ መሰዋት፣ ከፎቅ መፈጥፈጥ ስህተት ተብሎ ከተገኘማ አምባገንን ይቅርታ መጠየቅና መለማማጥ ስልጡን ፖለቲካ ሆኖ ታሪከን ያዋርዳል። ሕዝብን የጨረሰ ደርጉ ነው። ህይወትን የጠየቀቸ ደግሞ ድረሱልኝ ያለችው ውድ ሀገር ኢትዮጵያ ናት። ሌላ ሌላው ሁሉ ገጣሚው ገሞራው እንዳለው የማይታመን የቀመለ ወሬ፣ ውሸት ነው።

የአብዬን እከክ ለእምዬ ልክክ እንዲሉ፣ አህያውን ፈርተው ዳውላውን ቅጥቅጥ እንዲሉ የነበሩት ስርዓቶች በኤርትራ ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂ ሆነው ሳለ ኢሕአፓ ኤርትራን አስገነጠለ ብለው ሀሰትን ነጋ ጠባ የሚያናፍሱ ክፍሎች አሁን ም አሉ። እስከመቼ ይኽ ውሸት? የአፄው ስርዓት በኤርትራ የነበሩትን ሀገር አፍቃ ሪዎችና አርበኞች አግልሎ ባንዳዎችን ካቀፈ ና በተባባሩት መንግስታት የተወሰነው ን የፌዴሬሽን ትስስር ካፈረሰ በኋላ የኤርትራ ችግር የተባለው ተጋግሎ መከሰቱ

የማይቀየር ሀቅ ነው። በኦም ሀጀርና ሌሎችም ቦታዎች የተፈፀሙት ፍጅቶች ችግሩን አባባሱ እንጂ አልቀነሱትም። ደርግም ለስልጣን ሲበቃ እነ ጄኔራል አማን አንዶምን ሲገድል፣ ወጣቶችን በአስመራ በኮማንዶ አባሎች ሲያንቀና ሲያሳንቅ የጀብሀና ሻዕቢያን አባላት ቁጥር ጨመረላቸው። የራሱን ጦር ራሱ እያዳከመ፣ አዋጊ መኮንኖችን እየረሸነ፣ አልፎም በርካታ ጄኔራሎችን ገድሎ የጦሩን ሞራል በዚህም በዚያም ካዳከመ በኋላ ነገሩ አለቀለት ቢባል ምንም ክርክርን አይጋብዝም። የመንግስት ስልጣን ያልያዘው ኢሕአፓ ኤርትራን ሊገነጥልም ሆነ ሊያስገነጥል የሚችልበት ሁኔታ ምኔም አልነበረም። የኤርትራ ችግር ሲከሰትና ጀብሀ ሲመሰረ ት ሆነ በኦጋዴን ጦርነት ሲጀመር፣ ሜጫ ቱለማ ተቋቁሞና በባሌም አርሶ አደሩ ለትግል  ሲነሳ ወዘተ ኢሕአፓ ገና አልተመሰረተም ነበር። የብሄረሰብ ችግር በኢሕ አፓ የተወለደ ሳይሆን በስርዓቶቹ ግፍ የፈነዳ ነው። ኢሕአፓ ለዚህ ችግር መፍትሄ ጠቁሞ ኢትዮጵያውያንን በሀገር አንድነት ደረጃ በዴሞክራሲ ሊያነሳሳ ተነሳ እንጂ ሀሰተኞች እንደሚሉት ሀገርን ሊያስገነጥል አልተነሳም። የራስን ዕድል በራስ የመወ ሰን መብትንም ማወቁ በነበረው ርዕዮት መሰረት ተገቢውን መፍትሄ ያስገኝልኛል ብሎ በማመን እንጂ ግንጠላን ለመደገፍ ሆኖ በነበረማ ሁላችን እንገንጠል ካለው ወያኔ  ጋር ለምን ገና በ1967 አታካራ ይገባል፣ይጋጫል፣ይዋጋል? ለምንስ እንደ ወያኔ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ ፈርሞ ከሻዕቢያ ልክ እንደ ወያኔ አያብርም ነበር? ለምንስ ሩቡ ኢትዮጵያ የሶማሌ መሬት ነው ብሎ እንደ ወያኔ ከዚያድ ባሬ ተፈራርሞ ጥቅማ ጥቅምን አግኝቶ አይጠናከርም ነበር? ሀቅ ያንቃል፣ ሊደበቅም አይችልም። በኢሕአፓ ላይ የሚነዛው ሀሰት በየጊዜው እየተጋለጠም እርቃኑን ይቀራል።

ያ ትውልድ ራዕይ የነበረው ነውና፣ ለሕዝብ መብት ተቆርቋሪ ነበርና፣ ለውጥን ፈላጊ ነበርና ሀገር--በቀል ራዕይ አለን ብለው የመጡና ትግልንም የደፈሩ (ዛሬ ግን ለክሳቸው መድረክ ያገኙና የፈጠሩ) ያኔ ፀጥ በማለታቸው፣ባለመኖራቸው ወጣቱ ትውልድ የጊዜውን የሰፈነ የለውጥ ርዕዮት በመቀበልና ወደ ግራም በማዘንበል መፍትሄ ፈለገ። ዛሬ የሕዝብን መሰረታዊ ፍላጎትና ታሪክ ክደው ያ ትወልድ የባዕ ድ ራዕይ አምጥቶ ሀገር አተራመሰ የሚሉት ተማርን ባዮች በመሰረቱ የሚያንገበግ ባቸው ለምን የአፄው ስርዓት በትግል ፈረሰ የሚለው ነው። ለአፄው ስርዓት መንኮ ታኮት የታገለው ኢሕአፓ በዚህ ረገድ አጠፋሁ ተሳሳትኩ የሚለው የለውም። ኋላ

ቀርና ሕዝብን በድህነት ቀፍድዶና መብት ረግጦ የነበረ ስርዓት ነበርና፡፡ የደርግን ም አረመኔ ስርዓት በመታገሉ የሚቃጠሉ ክፍሎች ዛሬ በሰበብ አስባቡ ያን ቆራጥ ፀረ ደርግ ትግል ሊያንቋሽሹ ቢሞክሩም በመሰረቱ ውርደት በእኔ ይሆንባቸዋል እንጂ ሀቁን ሊቀይሩ አይችሉም፡፡ ለነገሩማ መሬት ለአራሹ ብሎ መጮህ፤ ድህነት ወንጀል አይደለም፤ደሀውም ይማር ብሎ መሰለፍ፤ የታጎሩ ሁሉ ይፈቱ ማለት፤ የሀ ገር ሉዓላዊነት ይከበር ብሎ መሟገት፤ ዘረኛውን ኢያን ስሚዝን ተቃውሞ ለዚምባ ብዌ (ያኔ ሮዴሽያ) ሕዝብ ነፃነት መሰለፍ፤ባህል ይከበር፤ በአርሶ አደሮች ላይ የተጣ ለውአላግባብ ከፍ ያለ ግብር ይሰረዝ፤ የሰርቶ አደሩ ሕዝብ መብት ይከበር ወዘተ ብሎ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን ማንሳት መን ላይ ነው ባዕድነቱ? ሀገር አፍራሽነ ቱ? ዛሬ ያ መጥፎ ስርዓት ሄደብን ወደቀብን የሚሉና አፋቸውን ሞልተው መሬት ለአራሹ መባሉ ሁሉን ችግር ፈጠረ የሚሉ የብዝበዛ ጠበቆች እንደሚሉት ሳይሆን ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ አርሶ አደርና  ብዙሀን ቆሞ በቆራጥነት ታግሏል፡፡ ዛሬም የወያኔ ጀሌዎችና ዘረኞች ያለውን አገዛዝ እያዳነቁና ዴሞክራሲ ሰፈነ ብለው ሲዋሹ አምርሮ የሚታገላቸው ለዚሁ ነው፡፡ ሀቅ የሕዝብ ወዳጅ እንጂ የጨቋኞች አጋር አይደለችም፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሊተረክ የሚገባው ቀና ታሪክ የሌላቸው ሁሉ ታሪክ ፀሀፊ ሆነዋል፡፡ መፅሀፍ መፃፉና አንባቢ ማግኘቱ በደፈናው መልካም ቢሆንም ውሸትን እንደ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ መተርተር ግን ጎጂ ነው፡፡ ክህደቱ ማፈርና መደበቅ ሲገባው መፅሀፍ ፃፍኩ ብሎ ኢሕአፓ የኤርትራን ጥያቄ የቅኝ ግዛት ነው አለ ብሎ ዋሸ፡፡ ሲኒማ ሰሪ ነኝ ያለው ግለሰብ ደግሞ ኢሕአፓ በዚህ በዚያ አለምክንያት ሰው ይገድ ል እንደነበር አስመስሎ ሲያቀርብ ሌላ ደራሲ ነኝ ባይ ደግሞ ኢሕአፓ ለአባልነት ሲያጭህ እምቢ ካልክ በጥይት ይገድልህ ነበር ብሎ ለፈረንጁ ሁሉ አግዚኦ በሉ ሲል ቀጠፈ፡፡ አንዳንዱ አውቆ ሲዋሽ ሌላው ደግሞ ባላወቀው ገብቶ ያማረበት መስሎ ይቀላምዳል፡፡ ውሸት ግን በዝቷል፡፡ በዘመን አመጣሽ ፓልቶክ በሚለው መድረክ በየቀኑና ማታው ስለ ኢሕአፓ የሚነዛው ሀሰት  እንደ ወያኔ ኤኮኖሚ በ10 በመቶ ሂሳብ በየሳምንቱ የሚያድግ ነው፡፡ ኢሕአፓ ለዓመታት የህብረት ጥረቶችን ሲያግዝና ሲደግፍ፤ ከሁሉም ድርጅቶች ጋር በእኩል ሲሰራ እየታየ፤ ለሀገር ሲል ካደሙትና ወንጀል ከፈፀሙበትም ጋር ሲያብር እያሳየ ፤ ኬሌሎች

ጋር ለፍቶ ለህልውና ያደረሰውን ህብረት በቅደሚያ ያደናቀፉት ሌሎች መሆናቸ ው እየታወቀ፣ ኋላም ያጻከሙት ሕዝብን የካዱትና ፓርላማ የገቡት ሁለት መሪዎ ች መሆናቸው ገና ሳይረሳ አንዳንዶች አሁንም ዛሬም ህብረቶች የሚፈርሱት ኢሕአ ፓ እኔ ያልኩት ካልሆነ ብሎ ወይም አልተባበር ብሎ ነው ብለው ይዋሻሉ:: ሀቁ ግን ሌላ ነው የሚያሳየው:: በማንኛቸውም የህብረት ጥረቶች ኢሕአፓ አንድ ድምፅ ይዞና የብዙሃኑን ውሳኔ እያከበረ መቀጠሉን ማንም ሊክድ አይችልም:: አባላ ቱም በተቻላቸው ህብረቶችን ሲደግፉ ቆይተዋል:: ስለዚህም በዚህ ረገድ በኢሕአፓ ላይ የሚነዛው ውሸት ሁሉ ምንዋ ውሸት በዛ ያሰኛል::

ኢሕአፓ አንዱና ዋነኛ መለያው ኢትዮጵያዊ መሆኑ ነው ማለትም ለጋራ ሀገራችን ሉዓላዊነትና እድገት የሚታገል ድርጅት ነው:: የኢትዮጵያን ጥቅም መቼም ቢሆን መቼ አሳልፎ ሰጥቶ አያውቅም:: በስልጣን ተደልሎ ሕዝብን አልከዳም:: ጥቅማ ጥቅም ብሎ ከባዕዳን ጋር ሀገርን በሚጎዱ አቅዋሞች ዙሪያ አልተሰለፈም:: ዛሬ በኢሕአፓ ኢትዮጵያዊነት ወይም ሀገር ወዳድነት ላይ ጥርጣሬ ሊፈጥሩ ላይ ታች የሚሉ ክፍሎች ውስጥ አብዛኞቹ ግን ባገኙት አማራጭና ቀዳዳ ሁሉ የራሳቸውን ጥቅም በማስቀደም ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጎን መቆማቸውን ወይም በነጥቅም መገዛ ታቸውን ያየነው ነው:: ኢሕአፓ ለደርግም ለወያኔም ቢያድር፣ ሻዕቢያ የፈለገውን ሁሉ ቢያሟላ ወይም ቢቀበል፣ ለሱዳንና ሶማሌ ቢገዛላቸው፣ ለአሜሪካና አውሮጳው ያን ቢጎነበስ፣ ቻይና ደርግን ደግፉት ስትል እሺ ጌታዬ ብሎ ቢቀበል ኖሮ ምናልባ ትም ዛሬ በአራት ኪሎ ቤተመንግስት የሚፈነጨው ኢሕአፓ ሊሆን በቻለ ነበር:: ግን ኢሕአፓነቱን፣ ሕዝባዊነቱን የሸጠ የቸረቸረ የስም ብቻ ኢሕአፓ ሆኖ ይገኝ እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም:: ዛሬም ቢሆን ሀገር ወዳድነቱን ቅድሚያ ባይሰ ጥ ኖሮና ሹመትና ገንዘብ ፈላጊ ቢሆን ኖሮ ከወያኔ ተደራድሮና ሕዝብን ክዶ እንደ ነ ሆድ አምላኩ አድርባይነት ሁኔታ ወያኔ ጫማ ስር ወድቆ ግላዊ ጥቅሞችን ባሟላ ነበር:: ኢሕአፓ ግን በማያጠራጥርና ባልተሸራረፈ መንገድ ኢትዮጵያዊና ፀረ ወያኔ በመሆኑ ለዚህ ዓይነት ክህደት አልተበገረም:: በመሆኑም የተያዙ አባሎቹ ደብዛቸ ው ይጠፋል እንጂ ለወያኔ ፍርድ ቤት ተብዬ ወግ እንኳን አይደርሱም:: ኢሕአፓ አንድ ኃያል መንግስት አለና እሱ ባዘዘን አንጓዝ ብሎ በሽንፈት አልሰገደም::

ኢትዮጵያዊ ኩራትና ክብርን ጠበቀ እንጂ፡፡ ይህን ሊሉ የሚችሉ ለመሆኑ ስንቶቹ ናቸው? ትላንት ትላንት ወዲያ ኢትዮጵያን ካደሙና ካዋረዱ አገዛዞች ጋር አልተቃ ቀፍንም ብለው እንደ ኢሕአፓ አፋቸውን ሞልተው የሚናገሩና የሚናገሩትም ሀቅ የሚሆን ለመሆኑ እነማን ናቸው? የኢሕአፓ አባላት ድርጅታቸውን የሚያፈቅሩት ኢትዮጵያ ሀገራቸውን ስለሚወዱና ኢሕአፓም ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ቆሟል ብለ ው ስለሚያምኑ ነው፤፤ ይህ መሰረታዊ ሀቅ የማይገባቸው ወይም በሀገር ወዳድነት ሽፋን የራሳቸውን ጥቅም ማስቀደም የሚሹ ክፍሎች ግን የኢሕአፓ አባላት ኢትዮ ጵያን ትተው ድርጅታቸውን ብቻ የሚወዱ አስመስለው ያቀርባሉ፡፡ ተደናግሮ ማደናገር ይሏል ይህ ነው፡፡ የኢሕአፓ አባላት የተሰባሰቡት በዓላማና መርህ ዙሪያ እንጂ አንድን ግለሰብ ፍፁም መሪ በማለት ወይም እንደ ጣዖት በማምለክ አይደለ ም፡፡ ስለዚህም የሆነ መሪ መርህን ጥሶ የግል ፍላጎቱንና ጥቅሙን አስቀድሞ ሲነሳ ብዙሃኑ አይከተሉትም፡፡ ኢሕአፓ ዘንድ አንቱታ ለሕዝብ ነው፤ የሕዝብ ጥቅም ከሁ ሉም በላይ ነው፤ ድርጅትም ሆነ መሪ ይህን እስከተከተለ ድረስ ይከበራል፡፡

በኢሕአፓ ላይ ውሸት የበዛው አንድም አዲሱ ትውልድ በሚገባ ሀቁን ስላልሰማ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ጠላቶች--የትላንትናና የዛሬም-- ይህን ኢትዮጵያዊ ድርጅት ለማጥፋት በመረባረባቸው ነው፡፡ ኢሕአፓ ግን በሀሰት ናዳ የሚሞት የሚጠፋ አለመሆኑን በቀጣዩ ትግሉ እያሳያቸው ነው፡፡ ውሸት ቢበዛ ሀቅን ሊገድል ሊያጠፋ አይችልም፡፡